# የአለርት-ታሪክ ባጭሩ

አለርት በብዙ ኢትዮጵያን ልብና አዕምሮ ውስጥ ዘወትር የሚታወስ ቃል ሲሆን፣ በአፍሪካ አህጉርም በጤናው ዘርፍ ስሙ የገነነ የተቋም ስያሜ ነው። በሀገራችን ቀደም ካሉ ጊዜያት ጀምሮ ከስጋ ደዌ ጋር ለተያያዙ የጤና ችግሮች መፍትሔ ሲሰጥ ኖሯል። በዚህ ዘርፍ ብቸኛው የህክምና የጥናትና ምርምር ማዕከል ሆኖ ለዘጠና አመታት ዘልቋል።

የአለርት ሆስፒታል በአዲስ አበባ ዘነበ ወርቅ በሚባለው አካባቢ ከፍ ባለ ቦታ፣ መልክዓምድራዊ አቀማመጡ ባማረ፣ በነፋሻማ አየር በታጀበ ሰፊ ጊቢ ውስጥ የተገነባ፣ በዕድሜው ለበርካቶች ጤናማ ህይወትን ያጎናፀፈ፣ የመኖር ተስፋን ዳግም ያለመለመ የፈውስ መንደር ነው።

አለርት ሆሰፒታል ከመነሻው ከስጋ ደዌ ጋር የተያያዙ የጤና እክሎችን ለማከም የተቋቋመ ቢሆንም፣ በሒደት ግን ለሁሉም ዓይነት ታማሚዎች አጠቃላይ የህክምና አገልግሎት የሚሰጥ ሆስፒታል ሆኗል። ከዛም በላይ በጤናው ዘርፍ የምርምር ስራዎችን ያከናውናል፣ የስልጠና አገልግሎትም ይሰጣል።

ከዚህ አኳያ ለጤናው ዘርፍ ብቁ ባለሙያዎችን በማፍራት ለሀገር ዕድገት ያበረከተው አስተዋፅኦ ወደር አይገኝለትም። የህክምና፣ የምርምርና የስልጠና አገልግሎት የሚሰጥ ተቋም ለመሆን እና እዚህ ላይ ለመድረስ ዘጠኝ አስርት አመታትን በመጓዝ በርካታ የስኬት ምዕራፎችን ተሻግሯል።

ቀዳማዊ አፄ ኃይለስላሴ የስጋደዌ ችግርን በዘላቂነት ለመከላከል፣ ህሙማኑም የህክምና እርዳታ የሚያገኙበትን መንገድ ለማምጣት በማሰብ አሁን ዘነበወርቅ እየተባለ በሚጠራው አካባቢ ለስጋደዌ ህሙማን አገልግሎት የሚሰጥ የህክምና ማዕከል መቋቋም እንዳለበት ወሰኑ። ሀሳባቸውንም ዶ/ር ቶማስ ላምቤ ለሚባል ሚስዮናዊ አጋሩት።

ዶክተር ቶማስ ላምቤ የንጉሱን ፍላጎት በመረዳት እንቅስቃሴ አደረገ። ከዛም በ**1924** ዓ.ም በዶክተሩ አስተባባሪነትና በኢትዮጵያ መንግስት ጥረት የስጋደዌ ህክምና ማዕከሉ ግንባታ እውን ሆነ። ከሁለት አመት በኋላም ይኸው የስጋደዌ ህክምና ማዕከል በንጉሱ ሴት ልጅ ስም ልዕልት ዘነበወርቅ መታሰቢያ ሆስፒታል ተብሎ ተሰየመ።

ሆስፒታሉ የስጋደዌ ህክምና አገልግሎት በመስጠት ላይ እያለ፣ እ.አ.አ በ**1965** ዓ.ም ይህንን የሰሙ የአፍሪካ መሪዎች ለንጉሱ አንድ ሀሳብ አቀረቡላቸው፡ የስጋደዌ ህክምና ሆስፒታሉ የአፍሪካ ማሰልጠኛ ማዕከል እንዲሆን የሚል። አፄ ኃይለስላሴም በሀሳቡ ስለተስማሙ፣ የዓለም አቀፉ የስጋደዌ ኮሚቴም ለዚህ ድጋፍ በመስጠቱ፣ የዘነበወርቅ ሆስፒታል የመላው አፍሪካ የስጋደዌ መከላከያና የስልጠና ማዕከል ተደረገ። ስሙም ከዘነበወርቅ ወደ አለርት ተቀየረ።

አለርት ማለት የመላው አፍሪካ የስጋደዌ ህክምና፣ የመልሶ ማቋቋምና ማሰልጠኛ ማዕከል ለሚለው የእንግሊዝኛ ትርጉም የተሰጠ አህፅሮተ ቃል ነው። በዚህ መልኩ አለርት፣ አህጉራዊ የማሰልጠኛ ማዕከል ለመሆን በቃ።

ከዚህ በኋላም፣ አለርት በ1981 ዓ.ም የዓለም ጤና ድርጅት የስጋደዌ ማሰልጠኛ ተባባሪ ማዕከል ሆኗል። ይህን መሰል አለምአቀፍ እውቅና ማግኘቱ ለዕድገቱ አወንታዊ ሚና መጫወቱ አልቀረም።
ሆስፒታሉ ከህክምና እና ስልጠና አገልግሎት ባሻገር የምርምር ስራዎችም እንዲያከናውን እ.አ.አ በ1970 ዓ.ም የአርማወር ህንሰን የምርምር ኢንስቲቲዩትን በመከፈት መንቀሳቀስ ጀመረ።
ከሀገራዊ የስጋደዌ ማዕከልነት ወደ አህጉራዊ ተቋምነትም የተሸጋገረው የአለርት ማዕከል፣ በስልጠና እና በምርምር ስራዎች በአፍሪካ እየተስፋፋ የመጣውን የስጋ-ደዌ የጤና ችግር ተፅዕኖን ለመቀነስ ትልቅ ሚና ተጫውቷል።
ማዕከሉ ከስጋ-ደዌ ህክምና አገልግሎት ጎንለጎን፣ በዚህ ዘርፍ የሚሰጠው የማስተማርና ስልጠና አገልግሎት ለሀገራችንና ለአፍሪካ ሀገራት በርካታ የጤና ባለሙያዎችን አፍርቷል። በስልጠና ፕሮግራሞቹ የቅድመ ምረቃና ድህረ ምረቃ ተማሪዎችን እየተቀበለ በብቃት ያሰለጥናል።
በጤናው ዘርፍ ላሉ ሐላፊዎች፣ መካከለኛ ባለሙያዎችና ለከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ተማሪዎችም እንዲሁም ዓለምአቀፍ ደረጃቸውን የጠበቁ የተግባር ስልጠናዎችን በመስጠት የላቀ ድርሻ አበርክቷል። በዚህም በተለያዩ የጤና ዘርፎች ሀገራቸውንና ህዝባቸውን በታማኝነት የሚያገለግሉ ብቁ ባለሞያዎችን በማሰልጠን ጉልህ ድርሻ አበርክቷል።
የአለርት ማዕከል ለከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የሚያደርገው ድጋፍ ተማሪዎቻቸውን በተግባር በማሰልጠን የተገደበ አይደለም። ተቋማቱ በስጋደዌ ምርምር ላይ የሚያተኩሩ ፕሮግራሞችን እንዲያስጀምሩም ድጋፎችን ሲሰጥ ኖሯል።
እንደ ምሳሌም፣ የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ በቆዳ ህክምና የድህረምረቃ ፕሮግራም እንዲጀምር ማዕከሉ ድጋፍ ሰጥቷል። ከዚህ አኳያ የአለርት ማዕከል በጤናው ዘርፍ የማይደበዝዝ አሻራ አኑሯል።
የአለርት ማዕከል በህክምና እና ስልጠና ዘርፎች ከሚሰጠው ውጤታማ አገልግሎት በተጨማሪ በምርምር መስኩም ከኢትዮጵያ አልፎ ለአህጉሪቱ የተረፉ ስራዎችን አከናውኗል።
በምርምር ስራው በስጋደዌ፣ በቲቢና በሌሎችም በሽታዎች መንስኤና መፍትሔ ዙርያ የሚያጠነጥኑ ሳይንሳዊ ፅሑፎችን በየጊዜው እያሳተመ ለተጠቃሚዎች ያሰራጫል። በማዕከሉ ከተዘጋጁት የምርምር ፅሑፎች መካከል፣ 12 አመታትን ፈጅቶ በሊፕረሲ ሪቪው ጆርናል ላይ የወጣው ፅሑፍን ጨምሮ በየጊዜው የሚወጡ ጥናቶች ይጠቀሳሉ።
የአለርት ማዕከል የአገልግሎት አድማሱን እንዲያሰፋ፣ የተገልጋዮችን ብዛት ለመጨመር፣ የአገልግሎት ጥራቱን ለማሻሻል፣ ተቋማዊ ብቃቱን ለማሳደግና አሰራሩን ለማዘመን የተለያዩ ጥረቶችን አድርጓል።
ከነዚህ መካከል በኢትዮጵያ ሆስፒታሎች ማሻሻያ ፕሮግራም መሰረት የአለርት ሆስፒታልን አሰራርና የአገልግሎት አሰጣጥ ጥራት ለማሳደግ የተደረገው እመርታዊ አካሔድ ተጠቃሽ ነው።

ማዕከሉ ለአገልግሎቱ መሻሻልና ማደግ ከሰው ሐይል ማፍራትና ማብቃት በተጨማሪ፣ በየጊዜው ወሳኝ የሆኑ የመሰረተልማት ማስፋፋትና የህንፃዎች ግንባታ አከናውኗል። ዘመናዊ የሆኑ የህክምና እና የስልጠና ቁሳቁሶችንም ማሟላት ችሏል።

የአለርት ማዕከል ከምስረታው ጀምሮ ራሱን የቻለ ተቋም ሆኖ፣ በጀቱን ከዓለምአቀፍ ለጋሾች እያገኘ ለረዥም ጊዜ የህክምና፣ የምርምርና የስልጠና አገልግሎት ሲሰጥ ከቆየ በኋላ በ**1994** ዓ.ም ጀምሮ የኢትዮጵያ መንግስት ተረክቦት በጤና ጥበቃ ሚኒስቴር ስር ይተዳደራል።

ከዚህ በኋላ ማዕከሉ ከምርምርና ስልጠና ስራዎቹ በተጨማሪ አጠቃላይ ሆስፒታል በመሆን ሁሉንም ዓይነት የህክምና አገልግሎቶች መስጠት ጀምሯል። በማዕከሉ የሚሰጡ የህክምና ዓይነቶች እንዲጨምሩ፣ የህክምና መስጫ ክፍሎች እንዲሰፉ እና በርካታ ዲፓርትመንቶች እንዲከፈቱ ተደርገዋል።

በኢትዮጵ የኤችአይቪ ኤድስ ቫይረስን ተፅዕኖ ለመቀነስ በሚደረገው ጥረት የአለርት ማዕከል የሚጫወተው ሚና ትልቅ ነው። የበሽታው መዛመት ያሳሰበው የጤና ጥበቃ ሚኒስቴር፣ ከ**2001** ዓ.ም ጀምሮ የአለርት ማዕከልን የኤችአይቪ ኤድስ የስልጠና የልህቀት ማዕከል እንዲሆን መርጦታል።

የአለርት ማዕከልም ሐላፊነቱን ተቀብሎ በመላ ሀገሪቱ ይህን የጤና ቀውስ ያስከተለውን ወረርሽኝ ለመከላከል የሚተጉ ባለሙያዎችን ለማፍራት ተከታታይ የአሰልጣኞች ስልጠና በመስጠት ስኬታማ ስራዎችን አከናውኗል።

በህክምናው ዘርፍ የአለርት ማዕከል አጠቃላይ ሆስፒታል በመሆን ሁሉንም ዓይነት የህክምና አገልግሎት እየሰጠ ቢሆንም፣ አሁንም በሀገሪቱ ብቸኛው አገልግሎት ሰጪ የሆነባቸው የህክምና አይነቶች አሉ።

በህክምና አገልግሎት አቅም፣ ብቃትና ዓይነት ፈጣን ዕድገት ያሳየው የአለርት ማዕከል በዓመት በአማካይ ከ**375** ሺህ በላይ ህመምተኞችን የማስተናገድ አቅም ፈጥሯል። በቀን ደግሞ በአማካይ ከ**1200-1500** ተጠቃሚዎችን ያስተናግዳል።

የአለርት ማዕከል በዘጠና አመታት የአገልግሎት ዘመኑ ጎብኝዎቹን ለጤና ችግሮቻቸው መፍትሔ ሳይሰጥ አይመልሳቸውም። ይህ ደግሞ የማዕከሉ መለያ በመሆን ለዚህ ዘመን ደርሷል።

በዘጠና አመታት ውስጥ የአለርት ማዕከልን የስኬት ጉዞ በብዙዎች ተመስክሯል። በተለያዩ ጊዜያት ዓለምአቀፍ ዕውቅናና ሽልማትም አሸንፏል። ማዕከሉ በህክምና፣ በምርምርና በስልጠና ዘርፎች በሚሰጠው አገልግሎት በሀገር ደረጃ የላቀ አፈፃፀም በማሳየቱ እ.አ.አ በ**2011** ዓ.ም የኢትዮጵያ ጤና አጠባበቅ ማሕበር የዋንጫና የሰርቲፊኬት ተሸላሚ አድርጎታል።

ከዛ በፊትም እ.አ.አ በ**1982** በስጋደዌ ህክምና እና ስልጠና የአለርት ማዕከል በአህጉር ደረጃ ላስመዘገበው ስኬት የዓለምአቀፍ የወርቅና የሜርኩሪ ሽልማት ሲያሸንፍ፣ እንደገና በ**2001** እ.አ.አ በህንድ መንግስት የጋንዲ አለምአቀፍ ሽልማት ተበርክቶለታል።

በአለርት ማዕከል ሰፊ ውብና ማራኪ ግቢ ውስጥ የተገነቡት ዘመናዊ ህንፃዎች እንደየ ዓላማቸው በአግባቡ የተዘጋጁ፣ የተደራጁና ጥራት ያለው አገልግሎት መስጠት በሚያስችሉ ዘመናዊ መሳሪያዎች የተሟሉ ናቸው።
ማዕከሉ ስራዎቹን የሚያቀላጥፍባቸው የተለያዩ በኮምፒዩተር የተደገፉ የዘመኑ ቴክኖሎጂ ባፈራቸው ቁሳቁሶች የተደራጁ ቤተሙከራዎች አሉት።
የሕክምና ባለሙያዎች፣ ሰልጣኞችና ሰራተኞች የህክምና፣ የስልጠናና የምርምር ስራዎቻቸውን በመረጃ የሚያስደግፉባቸው ደረጃቸውን የጠበቁ አብያተ መፅሐፍትም የማዕከሉ አቅም ማሳያዎች ናቸው። ሁሉም በዲጂታል ቴክኖሎጂ የተደገፉ በመሆናቸው ለአጠቃቀም ይመቻሉ።
የአለርት ማዕከል በዘጠና አመት ጉዞው ያካበተውን ልምድ፣ ያዳበረውን አቅምና የፈጠረውን በጎ ተፅዕኖ በመጠቀም፣ ራሱን ወደ አዲስ የዕድገት ምዕራፍ የሚያሸጋግርበት ሒደት ውስጥ ገብቷል። በጤናው ዘርፍ እጅግ ዘመናዊ የልህቀት ማዕከል ለመሆን የሚያስችሉትን ስራዎች በስፋት እያከናወነ ይገኛል።
ለነገ ያስቀመጠውን ራዕይና የቀየሰውን ግብ የሚያሳኩ ትላልቅ የመሰረተልማት ግንባታዎችና የማስፋፊያ በስፋት በመተግበር ላይ ናቸው። ከነዚህ ስራዎች መካከልም፣ በሁሉም መልኩ የተሟላ፣ የዘመናዊ ህክምና ተቋም ተምሳሌት የሆነ፣ ዘርፈ-ብዙ አገልግሎት ለመስጠት ታስቦ በጥበብ ዲዛይን የተደረገ፣ የባለ **500** አልጋ ሆስፒታል ይገኝባቸዋል። አሁን ግንባታው በመጣደፍ ላይ ነው።
በመሰራት ላይ ያለው ይኸው ግዙፍ የሆስፒታል መሰረተልማት፣ ዓለምአቀፍ ደረጃውን የጠበቀ ሁሉን አቀፍ አግልግሎት ለመስጠት የሚያስችሉት ዘመኑ ባፈራቸው የህክምና መሳሪያዎች የተሟላ፣ ሁሉንም ዓይነት የህክምና መገልገያዎችን ያሟላ፣ በዘመናዊና ትላልቅ ላቦራቶሪዎች የታጠቀ ይሆናል።
የአዳዲስ ህንፃዎች ግንባታና የመሰረተልማት ማስፋፋት ስራው፣ ማዕከሉ ከዚህ ቀደም ሲሰጥ የነበረውን የጥናትና ምርምር ተግባሩንም በበለጠ በጥራትና በብዛት ለማከናወን ያስችሏል።
በዕድሜው ያፈራውን እሴት በመጠቀም፣ በጤናው ዘርፍ ከፍተኛ እውቀት፣ ክህሎትና ልምድ ያካበቱ ባለሙያዎችን ማፍራትና በበሽታዎች ላይ መፍትሔ-ተኮር ምርምሮችን ማካሔድ አሁንም የአለርት ማዕከል ግንባር ቀደም ሐላፊነት ሆኖ ይቀጥላል። ግንባታውና የማስፋፊያ ስራውም ይህን ታሳቢ ያደረገ ነው።
የህክምና አገልግሎት ከሚሰጡ ተቋማት የሚጠበቀው፣ ሁለንተናዊ የግቢና የስራ አካባቢ ፅዳትና ውበት በአለርት ማዕከል ላቅ ባለ ደረጃ እየተሰራ ይገኛል። የስራ አካባቢው ለሌሎችም አርአያ በሚሆን መልኩ፣ በግቢም ይሁን በመገልገያ ክፍሎች፣ ለአይን በሚማርክ፣ ምቾትን በሚለግስ አኳሃን እየተከናወነ ነው።
ይህ እነቅስቃሴ ለማዕከሉ ማሕበረሰብ፣ ለታካሚውና ለሰልጣኙ ሁሉ አካላዊ ምቾትን ከመለገስ፣ መንፈሳዊ እርካታን ከማጎናፀፍና አዝናኝ ድባብን ከመፍጠር አኳያ ፋይዳው ትልቅ ነው።

የአለርት ማዕከል በዘጠና አመታት ጉዞው በሀገራችንና በአፍሪካ በጤናው ዘርፍ በብዙ መልኩ የሚመዘኑ አመርቂ ውጤቶችን አስመዝግቦዋል።

በእውቀትና በስነምግባር በታወቁ ከፍተኛ ባለሙያዎቹ በስጋደዌ፣ በቆዳ፣ በቲቢ፣ በኤች አይቪ/ኤድስ፣ በእናቶችና ህፃናት ጤና እንዲሁም በድንገተኛ አደጋዎች ህክምና፣ በሪሃብሊቴሽና በሌሎችም ተላላፊ እና ተላላፊ ባልሆኑ በሽታዎች ላይ በማተኮር የህክምና አገልግሎት ሲሰጥ ኖሯል።

በስልጠናው እና በምርምር ዘርፉም በዘመናት ሒደት ባካበተው ልምድና ግዙፍ አቅም በርካቶችን በማሰልጠን ለኢትዮጵያና ለአፍሪካ በርካታ የጤና ባለሙያዎችን አፍርቷል። በዚህም አለርት የአህጉሪቱ ባለውለታ ነው።

አሁንም  በአፍሪካ ቀዳሚና ጥራቱን የጠበቀ እውቅናና ተቀባይነት ያለው የህክምና፣ የምርምርና፣ የስልጠና ማዕከል ሆኖ የመገኘት ራዕዩን ለማሳካት እየገሰገሰ ነው። አሁን ያለው ዘመናዊ አካሔድና ግዙፍ የማስፋፊያ ስራም ለዚህ ምስክር ነው።